

# የእርስዎ የቆሻሻ፣ የቆሻሻ ዳግም ጥቅም ላይ ማዋል፣ የኮምፖስት እና ሌሎችም መመሪያ!

**ቆሻሻን ከቆሻሻ መጣያ ስፍራ ውጪ ስላስቀመጡ እናመሰግናለን።**




CITY OF CAMBRIDGE

THE WORKS CAMBRIDGE DEPARTMENT OF PUBLIC WORKS

ZERO WASTE CAMBRIDGE



ፎቶ፡- Kyle Klein

**የካምብሪጅ ከተማ ከ 2016 ጀምሮ ዓመታዊ ቆሻሻን በ 2,000 ቶን ቀንሷል።**

**በጋራ ሆነን፣ ሩቅ መጓዝ እንችላለን! ከምንጥላቸው ከግማሽ በላይ ቆሻሻዎች ዳግም ጥቅል ላይ ሊውሉ፣ ኮምፖስት ሊደረጉ ወይም ከቆሻሻ መጣያ ስፍራ ውጪ ሊቀመጡ ይችላሉ።**

# ሳምንታዊ የቆሻሻ መሰብሰብ አገልግሎቶች

---

**የካምብሪጅ Department of Public Works (DPW፣ የህዝባዊ ስራዎች መምሪያ) ሳምንታዊ ዳግም ጥቅም ላይ የዋለ ቆሻሻ፣ ኮምፖስት፣ የግቢ ውጋጅ እንዲሁም ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት ያቀርባል።**

- የቆሻሻ ማስቀመጫዎችን ከሚሰበሰብበት ቀን በፊት ባለው ምሽት ከ6pm በኋላ ወይም በሚሰበሰብበት ቀን እስከ 7am በመንገድ ዳር ያስቀምጡ።
- ከተሰብሰቡ በኃላ፣ የቆሻሻ ማስቀመጫዎችን እስከ 6pm ድረስ ከእግረኛ መንገድ ላይ ያንሱ።
- የቆሻሻ ማንሳቶች በበዓላት ምክንያት ሊዘገዩ ይችላል። የእርስዎ የሚሰበሰብበት መርኃግብርን ለማየት ድረገጻችንን ይጎብኙ።

**በሚከተለው ጊዜ የቀሩ ቆሻሻ ማንሳቶችን ሪፖርት ያድርጉ፡-** በመሰብሰቢያ ቀን ከ 4pm በኋላ ወይም ከተነሳ በኋላ በቀን 9am በ CambridgeMA.Gov/311።

**የቆሻሻ ማስቀመጫዎች፣ አቅርቦቶች ወይም ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ? CambridgeMA.Gov/Recycle**

# የእኛን "በትክክል ያስወግዱት" መሳርያን ይጠቀሙ

- በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ይፈልጉ!
- የሚሰበሰብበት መርኃግብርን ይመልከቱ እንዲሁም ማስታወሻዎችን ያዘጋጁ።
- ለልዩ መሰብሰቢያዎች (ትራሶች፣ የቤት እቃዎች፣ ጨርቃጨርቆች እና ሌሎችም) አቅጣጫዎችን ይመልከቱ።
- የመንገድ ላይ ማጽዳት መርኃግብርን ይመልከቱ።




መሳሪያውን ይጠቀሙ ወይም የ Zero Waste Cambridge መተግበሪያን በሚከተለው ያውርዱ፡-**CambridgeMA.Gov/Recycle**

# ቆሻሻ



- ✓ **በከተማ የተሰጡ የቆሻሻ ማስቀመጫዎች ውስጥ ቆሻሻን ያስቀምጡ።**
- ✓ **ከመጠን በላይ የሆነ ቆሻሻ በትላልቅ ከረጢቶች (ቢያንስ 3 mils ውፍረት ያለው) ውስጥ መቀመጥ ይገባዋል። በሚሰበሰብበት ቀን ጠዋት ብቻ ከቆሻሻ ማስቀመጫ ጎን ያስቀምጡ።**
  - ምግብ ነክ ነገሮችን መያዝ የለበትም።
  - ከረጢቶቹ ከ 50 ፓውንድ በታች መመዘን ይገባቸዋል።

# መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

ዳግም ጥቅም ላይ ማዋል በማሳቹሴትስ ውስጥ ግዴታ ነው።

## የብረት ጣሳዎችእና ፎይል



## የብርጭቆ ጠርሙሶች እና ማሰሮዎች



## የፕላስቲክ መያዣዎች



## ወረቀት እና ካርቶን (የተጠፈጠፉ ሳጥኖች)





**እቃው በዝርዝሩ ላይ የለም?**
በሚከተለው ዳግም ጥቅም ላይ መዋል ይችል እንደሆነ ያረጋግጡ፦
CambridgeMA.Gov/Recycle



**ምንም**የፕላስቲክ ከረጢቶች/ፊልም፣ መጠቅለያዎች አይፈቀዱም።




**ምንም** ምግብ ወይም ፈሳሾች አይፈቀዱም። መያዣዎችን በቀላሉ ያለቅልቁ።



**ምንም**ጎማዎች፣ ገመዶች፣ ማንጠልጠያዎች፣ ኤሌክትሮኒክስ አይፈቀዱም።

# ኮምፖስት

ኮምፖስት ማድረግ በቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች ያለውን ቆሻሻ ለመቀነስ ይረዳል እንዲሁም የአየር ንብረትን ይጠብቃል።

**ሁሉም የምግብ ትርፍራፊዎች...**



**... ስጋ፣ አጥንት እና ቅርፊቶች ሳይቀሩ!**



**የተቆረጡ አበቦች**



**ናፕኪኖች እና የመጸዳጃ ሶፍት**



**የቡና አተላ እና ማጣሪያዎች፣ የሻይ ከረጢቶች**





አይጦችን ለመቆጣጠር ምግብን **በተቆላፊ የኮምፖስት ማስቀመጫዎች** ማድረግ ከቆሻሻ ማስቀመጫዎችች የተሻለ ነው።





**ደረጃ 1**
የማዕድ ቤትዎን የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በኮምፖስት መያዣ ይደርድሩ እንዲሁም የምግብ ትርፍራፊዎችን ይሰብስቡ።



**ደረጃ 2**
ከረጢቱንበ መንገድ ዳር የኮምፖስት ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ እና ይቆልፉት።

**በህንጻዎ ላይ የኮምፖስት ማንሻ የለም?**
ነጻ የማዕድ ቤት ቆሻሻ መያዣ ማዘዝ እንዲሁም ከመጣያ ሰፍራዎቻችን በአንዱ የምግብ ቆሻሻን መውሰድ ይችላሉ።

የማዕድ ቤት ቆሻሻ መያዣ ይዘዙ እንዲሁም በሚከተለው ተጨማሪ መረጃ ያግኙ፦CambridgeMA.Gov/Compost

# አልባሳት / ጨርቃ ጨርቆች

የግዛቱ ህግ ጨርቃጨርቆችን ቆሻሻ ውስጥ መጣል ይከለክላል። ሁሉንም ጨርቃጨርቆች ይለግሱ፣ ለሌላ ስራ ያውሉ ወይም ዳግም ጥቅም ላይ ያውሉ።

• ልብሶች • አንሶላዎች • ፎጣዎች • ጫማዎች • መለዋወጫዎች

እቃዎች ሊቦጫጨቁ ወይም ሊቆሽሹ ይችላሉ፣ ነገር ግን ንጹህ እና ደረቅ መሆን አለባቸው።

ነጻ የቤት ለቤት ማንሳት መርኃግብር በሚከተለው ያስይዙ (ወይም የመጣያ መያዣ ይፈልጉ)፦ **CambridgeMA.Gov/Recycle**

---

# የትላልቅ እቃ ማንሳት

እንደ ሶፋ እና የልብስ ማስቀመጫዎች የመሳሰሉ አንዳንድ እቃዎች ፈቃድ አይፈልጉም። እንደ ትራሶች፣ ቲቪዎች እና የቤት እቃዎች የመሳሰሉ ሌሎች እቃዎች ፈቃድ ይጠይቃሉ። ፈቃድዎን በሚከተለው መርኃግብር ያስይዙ፦**CambridgeMA.Gov/Recycle**

እቃዎችን ለመለገስ ወይም ኦንላይን ላይ ለመለጠፍ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፦ NextDoor፣ Craigslist ወይም Facebook ቡድኖች ("Buy Nothing Cambridge"፣ "Curb Alert Cambridge")።

---

# የግቢ ቆሻሻ

- ✔ ከኤፕሪል 1 እስከ ዲሴምበር 31 ድረስ ይሰበሰባል።
- ✔ የወረቀት ከረጢቶችንወይም መያዣዎችን በከተማው ከተሰጡ ስቲከሮች ጋር ይጠቀሙ።
- ✔ የዛፍ ቅርንጫፎች እና ቀንበጦች ከ 3 ጫማ ያጠሩ መሆን ይገባቸዋል።

⊘ ምንም አይነት የፕላስቲክ ከረጢቶች ወይም አፈር አይፈቀድም።

የገና ዛፎች በጃንዋሪ የመጀመሪያ ሁለት ሳምንታት ውስጥ ይሰበሰባሉ።

# የዳግም ጥቅም ላይ ማዋል ማዕከል

አንዳንድ ቁሶች ለመንገድ ዳር ዳግም ጥቅም ላይ ማዋል ሊቀመጡ አይችሉም፣ እናም የሚከተሉትን ጨምሮ ወደ የዳግም ጥቅም ላይ ማዋል ማዕከል መወሰድ አለባቸው፦

- ባትሪዎች (አልካላይን ያልሆኑ)
- መጽሃፍት
- የፕላስቲክ ከረጢቶች
- የተቆራረጠ ብረት
- አነስተኛ ኤሌክትሮኒክስ (ከ 20 ፓውንድ በታች)።
- ፍሎረሰንት አምፖሎች




ማክሰኞ እና ሐሙስ፣ ከ 4pm–7:30pm፤ እና ቅዳሜ፣ ከ 9am–4pm ክፍት ነው።
147 Hampshire St. (ከ DPW Yard የጀርባ ቀኝ መታጠፊያ)።

---

# የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻ

አብዛኞቹ **አደገኛ፣ መርዛማ፣ አደጋ ያለው፣ ማስጠንቀቂያ ወይም ማሳሰቢያ** ተብለው የተሰየሙ ዕቃዎች በአደገኛ የቆሻሻ ኩነት ጊዜ መጣል ይገባቸዋል። ለቀናት፣ የሚከተለውን ይጎብኙ፦ **CambridgeMA.Gov/Recycle**

✔ **ተቀባይነት ያላቸው ዕቃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**

- ዘይት ያላቸው ወይም የላቴክስ ቀለሞች
- ኬሚካሎች
- መድኃኒቶች
- የፕሮፔን ታንከሮች
- የእሳት ማጥፊያዎች የመኪና ባትሪዎች
- ጎማዎች (እስከ 4 ድረስ)

🚫 አደገኛ ፈሳሽ ምርቶችን በፍጹም ወደ ቆሻሻ ውሃ መስመሮች ወይም የፍሳሽ ጉድጓዶች አያፍስሱ ወይም ቆሻሻ መጣያ ውስጥ አያስቀምጡ።

🚫 ኬሚካሎችን አይደባልቁ።

የካምብሪጅ ከተማ
**Department of Public Works**
147 Hampshire St
Cambridge MA 02139
617.349.4800

# ለቆሻሻ፣ ዳግም ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ለኮምፖስት እና ለሌሎችም የእርስዎ መመሪያ እነሆ!

በጋራ፣ ቆሻሻን ከቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች ውጪ ማድረግ እንችላለን።




2022/2023 መመሪያ ከአገልግሎት በኋላ ዳግም ጥቅም ላይ በሚውል ወረቀት የታተመ።